# አባ ባህሩ ናፈቁኝ

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)* *ታህሳስ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ብዙውን ጊዜ ዘመን ተቀየረ እያልን መጨዋወት እንጅ እድሜአችን ጨመረ እያልን መናገር አንቀጥ ይሆንብናል። ስለ እድሜ የማውራት ድፈረቱ ያለን አንዳንዶቻችንም ቢሆን እንደዚያ አይነቱ ወሬ ላይ ብዙ መቆየት አንፈልግም። መላ ቢጤ ፈጥረን ርእሷን እንደ ኮማንዶ ፈጠን ብለን ወደ ሌላ እንቀይራታለን። *ሰው ሲያረጅ ወደ ምድኛ፣ በሬ ሲያርጅ ወደ ሙኛ* ይባላል። አንዳንዴ እድሜዬ ከአመት አመት በአንድ በሁለት በሶስት … እየጨመረ በሄደ ቁጥር አእምሮዬ ተስፈንጥሮ ወደዚያው ወደ አገራችን ይበርና ሳድግ አይ የነበረውን በማስታወስ ሲያወጣ ሲያወርድ ይውላል። "ይህ ወጉን የሚጠርቅ ሰው አንድ ሐሙስ የቀረው የጃጀ ሽማግሌ ሳይሆን አይቀርም" እያላችሁ ስለማታውቁት ሰው የምታወሩ ካላችሁ ሳይታይ የሚያየው ይቅር ይበላችሁ ከማለት በስተቀር ሌላ እምለው የለም። እንደኔ ከሆናችሁ የፋሲካ፣ የመስቀል፣የገና፣የጥምቀትና ሌሎችም በአላት ሲቃረቡ በልጅነት ዘመን በቤትና በአካባቢያችሁ ይደረግ የነበረው ልዩ የማህበራዊና ባህላዊ ዝግጅት ትዝ ይላችኋል ብዬ እገምታለሁ። ለማንኛውም ቡናም ሆነ ሻይ ኮረንቴ ጨብጣችሁ "እህ…" እያላችሁ ለማዳመጥ ፈቃደኛ ለሆናችሁ የገናና ጥምቀት በአላት ሲቃረቡ ትዝ ከሚሉት አንዱ ቤተክርስቲያን ነውና የኔዋ እድሜም በአቅሟ በመስታወቷ ስላሳየችኝ የልጅነት የቤተክርስቲያን ትዝታ በትንሹ ላውጋችሁ።

እንደምታውቁት በአገራችን የቤተ-ክርስቲያን ግቢው ብቻ ሳይሆን አካባቢው ሁሉ በክብሩ ይፈራል። *"ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት"* የሚባለው ተረት እንግዳ እንደማይሆንባችሁ አምናለሁ። እንደምትገነዘቡት የሹመቱ ጉዳይ ሆድ ይፍጀው ተብሎ በትካዜ የሚታለፍ ቢሆንም ተረቱ ለታቦት በአገራችን ሲሰራ ኖሯል። በመሆኑም መጣፉ በሚያዝዘው መሰረት መለሎ መለሎው እንጨት እየተመረጠ ቤተ-ክርስቲያን ከአካባቢው ከፍ ወይም ጉብ ካለ ቦታ ላይ ይመሰረታል። አዎ መጽሐፈ-ኦሪት *"ለማደሪያው የሚቆሙትን ሳንቆች ከግራር እንጨት አድርግ። የሳንቃውም ሁሉ ርዝመት አስር ክንድ፤ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን። …መጋረጃውንም ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊም ከቀይም ግምጃ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታም አድርግ ወዘተርፈ…"** እያለ በሚያዝዘው መሰረት ሐዲስና ብሉይን እንደእንጀራ አኝከውና አድቅቀው በበሉ የቤተ-ክህነት ምሁራን ንድፍ-አውጪነትና በወንዝ በቀል አናጢዎች መሐንዲስነት ይሰራል። በእውነቱ እኔ የክህነት ማይሙ ከመሐራ ሰፈር ብቻ ሲያውደለድል ኖሮ በመቅቡጥ፣ በዝምድና ወይም በሌላ በሌላ አቋራጭ መንገዶች እንደተካነ ካህን ላይ ላይዩን እየነካካሁ በትዝታ መልክ አቀረብኩት እንጅ ባለሙያዎች ከንፈሩ ዘርዘር ያለ ጽዋን ወገብ ጨብጠው ሲያወጉት በቅቤ ካብደ የባለሙያ ሽሮም የበለጠ ይጥማል። አዎን ምእራፍና አንቀጥ እየጠቀሱ፣ በመካከል በመካከሉ ደግሞ የግእዝ ቃላትን እንደ ቋንጣ ጣል ጣል እያደረጉ ከዚያም መልሰው እየተረጎሙ፣ ፊታቸውን ኮስተር መልሰውም ፋታ እያደረጉ በስሜት ተውጠው ሲያወጉ ጆሮን ከፊት ቀልብን ደግሞ ከመሬት ላይ ያስጥላሉ።

ከቤተ-ክርስቲያን ግቢ መሐከል ክብ ሆኖ ከተሰራ የሚያምር የጠቢያ ቤተ-ክርስቲያን ዙሪያ ሕዝብ ተንበርክኮ አምላኩን የሚነጋገርበት፣ እየተነሳ እየወደቀ የሚለማመንበት፣ እጆቹን ወደ ፈጣሪ ዘርግቶ "ክርያላይሶ …፣ ወ… አምላክ.." እያለ የሚማጸንበት፤ "በእይንተ-ማርያም መሓርነ" እያለ በጣቶቹ አስራ ሁለት ጊዜ የሚቆጥርበት፤ አገራችንን ጢቢያን ባርክ እያለ በቀጠነ ድምጽ የሚማጸንበት፤ ተረኛውም ካህን ከፊታቸው ምላሱን ጎልጉሎ በቆመው የቆሎ ተማሪ ምራቅ አመልካቾ ጣታቸውን እያረጠቡ ታምረ-ማርያም የሰፈረበትን ብራና እየቀያየሩ የሚያነቡበት፤ ራሳቸውን እንደ አውሎ ነፋስ ቀጥ ብሎ በሚቆም ጥምጣም የሸፈኑ ቄስም በአራቱ ማእዘን አማትበው መክለፍት የሚቆርሱበት፤ አቃቢ መነኩሳት ቆባቸውን በአናታቸው፣ እባኔአቸውን ደግሞ በአንገታቸው ጣል አድረገው የተባረከውን መክለፍት "ስለ እለተ-ሰንበት!" እያሉ ለሕዝብ የሚዘክሩበት፤ የእለቱ ሰባኪም አንዴ በተረከዛቸው ሌላ ጊዜም በእግር ጣቶቻቸው ቆመው ሽንጣቸውን ወደ ላይ እየሳቡና እጃቸውን እንደ ዘንግ እየሰበቁ "በዚያች ቀን ወዮልህ…" እያሉ ምእመናንን የሚያስጠነቅቁበት የተዘጋጀ ስፍራ በቤተ-ክርስቲያኑ ዙሪያ ይኖራል። ብዙም ሳይርቁ ይህች አለም በቅታቸው አለዚያም "በቃችሁኝ!" ብላቸው መቃብር ውስጥ የገቡ ሙታንን ሲጠብቁ ውለው የሚያድሩትን እንደ ግራር፣ አንፋር፣ ሰንሰል፣ ውልክፋ፣ ሐረግ ወዘተ የመሳሰሉትን ዛፎች በዘርና በክልል ተከፋፍለው ሳይሆን በሰከነ መንፈስ እርስ በርስ ተቆላልፈውና ተቃቅፈው ሲኖሩ ያስተውላሉ።

የአላደገበት ሰው ወደ ቤተ-ክርስቲያን ግቢ ሲገባ የሚሰማውን ስሜት እኔ እንጃ። እኔን ሆኖ ወይም እኔን መስሎ ላየው ግን ገዳሙ ራሱ ይቅርና ገዳም ሰፈርም ሲገቡበት ደስ የሚል ፍርሃት በሰራ አካላት ላይ ይረጫል። " ምን መዘባረቅ ነው! ደሞ ከፍርሃት ደስታ ሲመነጭ የት አገር ነው ያየህ!" ብላችሁ አፋ አፌን አትበሉኝ። አዎ ከእንደዚህ አይነቱ ጸጥ ካለ የአምልኮት ቦታ ሲገቡ በግልጥም ሆነ በድብቅ ሲፈጽሙ የኖሩትን ተንኮል፣ ክፋት፣ ማጭበርበር፣ ስርቆት፣ ቅጥፈት፣ አስመሳይነት፣ ክህደት፣ ቅናትና ሌላም ሌላም ሐጥያት እየተመለከተ "አንተ ነፍሰ-ገዳይ፣ አንተ ቀጣፊ፣ አንተ አጨበርባሪ-ሞላጫ፣ አንተ የግፍ ቋት፣ አንተ ከንቱ የሰይጣን- መላክተኛ ወዮልህ" የሚል መንፈስ የሚወር ይመስልና የፍርሃት ማጥ ውስጥ ይለቃል። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ተግሳጽ ለማጽዳት እንጅ ለመቅጣት ወይም ለመበቀል ስለማይመጣ ደስ ይላል። ታዲያ ይህችን

ግፍ እንደ ስንዴ የሚዘራባት ከንቱ አለም በቃችኝ ብለው፤ ይህንን ትናንትናም ዛሬም እኛን የሚያፋጀንን መንበረ-ስልጣን፣ ገንዘብ፣ ሆድና ስስት ሰበሰብ አርገው በሳት አቃጥለውና አመዱንም ሰይጣን ከማያገኝበት ቦታ ቀብረው፤ ከእንዲህ አይነቱ እኛ ለመግባት እንኳን ከምንፈራው ገዳም ውስጥ ብቻቸውን ይኖሩ የነበሩ አባ ባህሩ የሚባሉ መነኩሴ በልጅነት ዘመኔ አውቅ ነበር።

አባ ባህሩ የመነከሱት ገና በሃያዎቹ እድሜ ውስጥ ነው ይባላል። እኔ ሳውቃቸው እድሜአቸው ምናልባት ወደ ሰላሳዎቹ መጨረሻ የሚጠጋ ይመስለኛል። ከራሳቸው የማይለዩት ቢጫ ቆቦቻቸው ዛሬም ከአይኔ ላይ ናቸው። ከላይ ከጆሮዎቻቸው መባቀያ የሚጀምረው ጺማቸው ሰፋ ሰፋ እያለ በረጅሙ ፊታቸው ላይ ሲጓዝ ያድርና ሊነጋ ሲል አንገታቸውን ተሻግሮ፣ ከደረታቸው ላይ አርፎ ጭንፋር ይላል። ረዘምና ሰፋ ያለው አካላቸው የሚንቀሳቀሰው አብሯቸው ተፈጥሮ ባደገው ሌጣ እግራቸው ሞተርነት ነው። ቀና ብሎና ትኩር አድርጎ ለማየት ክብራቸውና ሌላም ለመግለጽ የሚያስቸግር ከላያቸው ላይ የሰፈረው መንፈሳዊ ሐይል ስለሚያስፈራ ስለ ተክለ-አካላቸው ከዚህ በላይ ለማለትና ለማብራራት ያስቸግራል። የሚያጥበረብር የብርሃን ሐይል ያላቸው ይመስል እርሳቸው ብቅ ሲሉ ሁሉም አይኑን ገርበብ አድርጎ አንገቱን ይደፋ ነበር። እርሳቸውም ከሚረግጡት መሬት በስተቀር ወዲያ ወዲህ ብለው የሚመለከቱት ነገር አልነበረም። ከሚያገለግሏቸው ምእመናን ጋር የሚተያዩት ልብ ለልብ ነበር ለማለት ይቻላል። ብቻ እገሌ ከእገሌ ሳይባል በነቂስ ከአካባቢው ሕዝብ ፍቅርን፣ ክብርና ተደማጭነትን ደርበው ደራርበው የተጎናጸፉ ቅዱስ ሰው በሕይወቴ እማውቀው አባ ባህሩን ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ አባ ባህሩ ታረቁ ብለው ያልተፈጸመ እርቅ፣ አባ ባህሩ አትፈጽሙ ብለው የተፈጸመ ድርጊት፣ አባ ባህሩ ይሁን ብለው ያልሆነ ነገር የለም።

“መንኩሰ ሞተ” የሚባለው አባባል ትክክል ነው ብዬ ተቀብየው የኖርኩት አባ ባህሩንና የእኔን የሴት አያት በማየት ነበር ለማለት እደፍራለሁ። አባ ባህሩን ስናያቸው ይሰማን የነበረው ለመግለጽ የሚያስቸግረው ስሜት “እግዚአብሔር በውክልና በዚያ ቦታ ላይ ተቀመጡ ብሎ የላካቸው የሕዝብ ጠባቂ እረኛ ናቸው” ስትሉ እመኑ ብሎ ያስጨንቀን ነበር ብዬ ለመናገር እቃጣለሁ። ዛሬ ዘወር ብዬ ሳየው አባ ባህሩ ከመላእክት የሚለዩት ስጋ በመልበሳቸውና ስጋቸውን በምድር ላይ ለማቆየት እህልና ውሃ በመቅመሳቸው ይመስለኛል። ለነገሩ ምግብም ይቀምሳሉ ሲባል ሰምቼ፤ እንደዚሁም ሳይበሉ ሳይጠጡ እንዴት ይኖራሉ በሚል አስተሳሰብ እንጅ እህል ሲቀምሱም ሆነ ውሃ ሲጠጡ አይቻቸው አላውቅም ነበር። እኔ እማውቀው “ምንም ነገር አታምጡ፣ ከእኔ ይልቅ በሰፈር በመንደራችሁ የተራቡ የተጠሙትን ታደጉ!” እያሉ ሲገስጡ ነበር። በአንድ ክብረ-በዓል ቀን ከሚኖሩባት ገዳም ውስጥ ካለች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ከእናቴ ጋር የሚቀመስ ነገር ይዘንላቸው ሄደን ለተራቡ ለተጠሙ ወፎች ስጡት ብለው እንደመለሱን አስታውሳለሁ። አልኮል ነገር ይቅርና ስጋና ወተትም ቀምሰው አያውቁም ይባላል። ሰው እንደሚለው ከሆነ ከረጅም ጸሎት በኋላ አንዳንዴ የሚቀምሱት ከዚያች ጨለማ ከዋጣት፣ ግራርና ሰንሰል ውስጥ ዘመም ብላ እንደ ነገሩ ከቆምች ጎጆ ጀርባ ካበቀሉት ቲማቲምና ጎመን እየቀነጠሱ ነው ሲባል እሰማ ነበር።

በየተራራው፣ በየዋሻውና በየደብሩ ባሉት የቅኔ፣ የዜማ፣ የድጓና ሌሎችም የቤተ-ክህነት ት/ቤቶች የታሪክና የመልከአ-ምድር(ጆግራፊ) ትምህርት ይሰጥ አይሰጥ የማውቀው ብዙም ነገር የለም። የት እንደተማሩት ባለውቅም ያለማጋነን አባ ባህሩ ጆግራፊ ካስተማረኝ አንድ ከሕንድ የመጣ መምህር እነደዚሁም ከአንዳንድ የራስ-ዳሽን ተራራን ከፍታ ከማወቅ ባሻገር ብዙም ዘልቀው ከማይሄዱት አሁን አሁን “የድንጋይ ማምረቻ” ከሚባሉ ኮሌጆች ከሚመረቁት መምህራን ባቻ ሳይሆን ከድሮዎችም ቢሆን በጣሙን የሚልቁ  ይመስለኛል። ስለ እያንዳንዱ የእስያ አገሮች፣ የድሮ ስሞቻቸውና ታሪካቸው በሚገባ ያትታሉ። ስለመካከለኛው ምስራቅ፣ ስለ ጣልያን፣ ስለ ግሪክና ቱርክማ ሲያዎሩ እዚያው ሄደው ያጠኑት ነበር የሚመስሉ። ስለ ጦቢያ መልከዓ-ምድርና ታሪክ የሚተርኩትማ ከአንደበታቸው ብቻ ሳይሆን ከአጥንታቸውና ከደማቸው ውስጥም የሚፈልቅ ነበር የሚመስለው። እንዲያውም እርሳቸውን ያዳመጠ ሰው ከአገዛዝ ጫካ ውስጥ የሚታተሙ፣ በቅጥፈትና በአድሎ የተሞሉ እንደ አዲስ ዘመን ካሉ ጋዜጦችና ከገዥዎች ወንበር ስር ከሚበተኑ ክታቦች እየጠቀሰ የሚጽፍን “ታሪክ ጸሐፊ” ወይም አስተማሪ ሲያዳምጥ ራሱን መታመም ብቻ ሳይሆን ሆዱንም እንደመጣላት ሊለው ይችላል ብየ አስባለሁ።

በቤተ-ክርስቲያኗ ሥርዓት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ሳድግ መነኩሴ መቅደስ ገብቶ ሲቀድስ አይቼ አላውቅም ነበር። አባ ባህሩንም ወደ መቅደስ ሲገቡ አይተናቸው አናውቅም ነበር። እንዲያውም ብዙን ጊዜ ከሕዝብም አይገናኙም። አንዳንዴ ብቅ የሚሉት ለሕዝብ የሚያስተላልፉት ጠቃሚ መልእክት ካለ ብቻ ነበር። ሳይንስን እንደ አገዳ መጥጫለሁ፣ የተፈላስፍኩ፣ የተራቀቁ ነኝ እያለ ፊኛውን እንደ ፈረንጅ የልደት ቀን “ባሎን” ለሚነፉና አውራ ጣቶቹን እርስ-በርሳቸው እያፍተለተለ ለሚደስኩር ግለሰብ ለመቀበል አስቸጋሪ ቢሆንም፤ አባ ባህሩ ወደ ፊት የሚከሰት ነገር የሚታያቸው የነብይ አይነት ባህሪ የነበራቸው መነኩሴ ይመስሉ ነበር። “በዘመነ-ማንትስ ድርቅ ሊመጣ ይችላልና ተዘጋጁ” ይላሉ። ዘመነ-ማንትስ ሲጠባ ድርቅም ተከትሎ ከተፍ ይላል። “በዚህ ጊዜ ወንበዴ ሌባ እንደ አሸን ይፈላልና ንብረታችሁን ጠንቀቅ ብላችሁ ጠብቁ” ብለው አበክረው ይናግራሉ። በተነበዩት የጊዜ ገደብ ውስጥም አይን ያወጣ ዘራፊ-ሌባ ባገር በመንደሩ በጠራራ ፀሐይ መትመም ይጀምራል። “በዚህ ወራት የአይጥ መአት ይፈላል” ብለው ያስጠነቅቃሉ። ወቅቱ ሲመጣ ሰብሉ፣ መንደሩና ጓዳው ሁሉ በአይጥ ወረርሽኝ ይጥለቀለቃል። “ልጆች እናታቸውን የሚከዱበት፣ የሚያራቁቱበት፣ የሚያስለቅሱበትና አሰቃይተው

የሚገሉበት ጊዜ ይመጠል" እንዳሉም ትንሽ ትንሽ ትዝ ይለኛል። ይኸው የኢትዮጵያውያን እናት ልጆቿ በክህደት እርስበርሳቸው እየተላለቁ ፊቷን እየላጠች አልቅሳ አልቅሳ አቅሟ በማለቁ ጣረሞት ላይ ያለች ይመስለኛል።

ብዙው ሰው የአባ ባህሩን የአባት ስም አያውቅም፤ አይጠይቅምም ነበር። እኔም እስከዛሬ የአባታቸውን ስም በትክክል አላውቅም። ሰዎች ግን የእነ እገሊት ወንድም፣ የእነ እገሌ ዘመድ ናቸው ሲሉ እሰማ ነበር። ዘመዶቻቸውም ቢሆን አባ ባህሩን የእኛ ወንድም ወይም ዘመድ ናቸው ሲሉ እምብዛም አልሰማም ነበር። ለምን እንደሆነ አሁን አሁን ሲገባኝ መነኩሴ መንፈሱ ስጋውን አድቅቆ የገዛው ሞቶ የሚሄድ ስጋ የተሸከመ ጻድቅ፤ ሁሉን ፍጡር በእኩል ሚዛናዊ አይን የሚያይ እግዚአብሔር እንደ መላእክት በውክልና የላከው የሕዝብ እረኛና አባት ስልሆነ ነው ብዬ አስባለሁ። በእኔ እምነት አባ ባህሩ ከአምላክ የታዘዙትን ትእዛዝ የሚያከብሩና የሚተገብሩ ስለነበሩ፣ ሁሉን በእኩል ሚዛን ስለሚያዩ፣ የስጋ ዘመዶቻቸውን ጨምሮ ሕዝቡም ይህንን በሚገባ ስለሚገነዘብ፤ እርሳቸው ሁሉንም ልጅ አድርገው ሲንከባከቡት እንደኖሩት ሁሉ፤ ጠቅላላው ሕዝብም ከልጅ እስከ አዋቂ እንደ አባት በመቁጠር ቀና ብሎ ሳያይ ያሉትን ሁሉ ሲፈጽም፤ ሲያከብራቸው፣ ሲወዳቸውና በአምላክ መልክም ሲያያቸው የኖረ ይመስለኛል።

ሆድ እንደባሰኝ ስላወቃችሁ እየኮረኮራችሁ ስለ ዛሬ ዘመን ምንኩስና ልታናግሩኝ አትሞክሩ። ከኔ ዶማ ኮቢ ይልቅ በአገር ቤት ከተሞችም ሆነ በውጩ አለም የተበተኑት የዛሬ መነኩሴዎች ተክለ-ቁመና፣አኗኗር፣ ምግባርና ከሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት አሳምሮ ስለሚገልጠው በጦቢያ አምላክ ይዣችኋለሁ እኔን ለቀቅ አርጉኝ። አዎ እኔን ለማውጣጣት ከመሞከር ይልቅ ጎበዝ ከሆናችሁ በየከተማችሁ ያማረ ካባቸውን ደርበው፣ ቄንጥ ያለው ቆባቸውን ደፍተው፣ እንደ እበነበረድ ከሚያበራ ሕንጻ ውስጥ የሚኖሩትን፣ እንደነ ሚካኤል ላሉ መላእክት፤ እንደነ ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ላሉ ቅዱሳን የሚበረከተውን ስለት እሞጨለፉ በሉመዚንና በሌሎችም አይነት ዘመናዊ አውቶሞቢሎች የሚተሙትን፣ አስራት እየከፈለ ቀልቧቸው የሚያድር ሕዝብ በኑግፍ አይፈሬ በጠራራ ፀሐይ በባሩድና በቆመጥ እንደ ቅጠል ሲረግፍ እንኳን ተግሳጽ መስጠት ጸሎትና ፍታት እንኳን የሚከለክሉትን፣ አድኑበት ተብለው በተሰጡት መስቀል እርስ በርስ ሲከሳከሱና ምእመናንንም ሲያናክሱ የሚውሉትን፣ ከገዳይ ለማምለጥ ገዳም ውስጥ እግዚአብሔርን እጉም ያሉ ምእመናን አሳልፈው የሚሰጡትን፣ ሕዝብ ፊት ሲቀርቡም እንደ አሜሪካው ፕሬዘዳንት በጫማ እንደዚሁም መልኩ በወዝዞ እንቁላል የሚጠፈጠፉትን መንፈስ-ቅዱስ፣ ክብርና ማእረግ የራቃቸውን "አባዎች" ተመልከቱ።

እንደዚህ አሁን በእኛ አገር እንደሚታየው ከሶስት መቶ አመታት በፊት በፈረንሳይ አገር ሰው ሰውን እየቆረጠመ በመብላት ላይ ይግኝ ነበር። የሚገርመው ነገር መስቀላቸውን ተሸክመው የሚውሉት አብዛኛው ካቶሊካዊ ካህናትም ከተበይው ሳይሆን ከቆርጣሚው ጋር ተሰልፈው ነበር። ፈረንሳይን ከእንዲያ አይንቱ ማጥ ውስጥ እንድትወጣ በሰላ ብዕር ከተፋለሙት ውስጥ ቀዳሚነቱን ስፍራ የያዘው ቮልቴር የተባለ በአለም ላይ የታወቀ ፈላስፋ ነበር። በኢፍትሐዊነት ላይ ነበልባል ብዕሩን ያነጣጠረው ቮልቴር *"አንድ አገር ወይም አንድ ሕዝብ ማሰብ ወይም ማወቅ ከጀመረ የፍትህ ባለቤት ለመሆን የሚያግደው ሐይል ፍጹም አይኖርም"* የሚል እምነት ስለነበረው እንደ እውነተኛ መነኩሴዎች ሁሉ ራሱን ከምድራዊ ጥቅም አላቆ ጣቶቹ ውኃ እስከሚቋጥሩ ይጽፍና ያስተምር ነበር። በዚህም ምክንያት ቮልቴር በዘመኑ በነበሩ ሰው በላ ገዥዎች ደጋግሞ ለእስራት ተዳርጎ ነበር። ለበርካታ ጊዜም ወደ እንግሊዝ፣ ጀርመንና ሌሎችም አገሮች በስደት እንዲኖር ተገዶ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንድ በጥቅማቸው የመጣባቸው የፈረንሳይ ካህን ከያእቆብ መልእክት *"እርስ በርሳችሁ ሀጥያታችሁን ተናዘዙ(ምዕ ፭:፲፮)"* የሚለውን ከጠቀሱ በኋላ "የሰረሃውን ጉድ ሁሉ በዝርዝር ተናዘዝ" ብለው ቮልቴርን ጠየቁት። እርሱም ሐጥያት ይሁንም አይሁንም የሰራውን ሁሉ አንድ በአንድ ነገራቸው። እርሳቸውም ያው እንደተለመደው *"ይህንን የሰርሃውን ሃጥያትህን ሁሉ ይቅር ይበልህ!"* ብለው ጸሎት አድርሰው ሊሄዱ ሲነሱ ያዝ አድርጎ እንዲቀመጡ ካደረገ ብኋላ ራሳቸው ደግሞ እድሜ ልካቸውን የሰሩትን ሃጥያት ሁሉ ለሱ እንዲናዘዙ ጠየቃቸውና አረፈው።** የናንተን አላውቅም እኔን ግን ቮልቴር ለፍትህ ባለው ፍቅር ባቻ ሳይሆን በጀግንነቱም ይበል፣ይሁን፣አሚን አሰኘኝ።

አንድ የአሁን ዘመን ምንኩስናን በሚገባ አስተውሎና ተገንዝቡ ቆሽቱ እንደ ማረር ያለ ጎበዝ የአባ ባህሩን ጉዳይ ካጫወትኩት በኋላ " አባ ባህሩ እንኳን አንተን እኔን የማላውቃቸውንም ናፈቁኝ!"አለና በረድ ብሎ በነበረው የፍቆት ምድጃ ውስጥ ሳንባ አርከፍክፎ እሳቱን አያይዞ በልቤ የተጣደውን ናፍቆት አፍለቀለቀው። አዎ ልቤ ፍስስ፣ አንጀቴም ልውስ እስከሚል ድረስ እኒያ የሞተ ሥጋ ተሸክመው የሚሄዱ ጻድቅ፣ እኒያ የሁሉ አባትና ጠባቂ የሆኑ አባ ባህሩ፤ እርሷ ያላገኘችውን እድል ለኔ ፈጥራ፣ እርሷ ሳትቀምስ እኔን እየመገበች፣ የመቀነቷን ቋጠሮ እየፈታች ስሙኔና ሽልንግ እየሰጠች ያስተማረችኝን፣ ለህልውናየ ለእድገቴና ለአሁኑም ኑሮዬ መሰረት፣ ግርግዳና ጣራ የሆነችውን የእናቴን ያህል ናፈቁኝ። እውነቴን ነው የምላችሁ ግራና ቀኝ ተመልክቼ እንኳን የሚስተካከላቸው የሚመስላቸውም መነኩሴ ሳጣ እንደ እኛ እናት እንደ እቴቴ ሁሉ አባ ባህሩ እጅግ ናፈቁኝ!

*ዋቢ*

*ኦሪት ዘጸአት ምዕ ፳፩:፲፩-፴፯* ** Will Durant, The Story of Philosophy